# የአማራ ፋኖ ድምፅ
# The Voice of Fano

በወቅታዊ አርዕስት በአፋሕድ የፖለቲካ ጉዳዮች መምሪያ እየተዘጋጀ የሚቀርብ
Issued by AFPO Department of Political Affairs on Current Topics

Vol. 1; No. 1
አንደኛ ዓመት የመጀመሪያ ቅጽ

Wednesday, August 20, 2025
ረቡዕ ነሐሴ ፲፬ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.


## Editorial

### AFPO Statement on Education and the Ethiopian New Year 2018

Call for Uninterrupted Continuation of Schooling and a Call for Global Support

**Issued by:** Amhara Fano People's Organization (AFPO)
**Date:** August 20, 2025
**Location:** Ethiopia

Education and schools serve as vital institutions of psychological support for children exposed to the hardships of war. For those who cannot yet think independently, schools provide not only knowledge but also guidance, encouragement, and examples of resilience. It is therefore essential to ensure access to education for all Amhara children, even under the most difficult circumstances.

Over the past two years, the oppressive and anti-Amhara regime has turned the Amhara region into a battlefield. As a result, millions of Amhara children and youth have been forced out of school, left to endure severe psychological trauma, and risk being lost as an entire generation. The regime has not only bombed schools with outdated and heavy weaponry but also converted many of them into military camps, looted educational materials, and deliberately sought to keep the Amhara people in ignorance and backwardness through prolonged war.

If this continues, when the war ends and a new system emerges, there will be no educated generation ready to lead social reconstruction. Tomorrow will only reflect what is sown today.

History provides lessons: during Hitler's persecution, Jewish children in Europe, even while fleeing and hiding in forests, continued their education in makeshift schools dug into the ground. Despite daily airstrikes, they preserved their studies because they believed that schools were the guardians of their people's values. Likewise, we must understand that education is more than learning to read, write, and count—it is the foundation of cultural survival, strength, and continuity.

The government-led war against the Amhara is not only about killing and displacement; it is a deliberate attempt to sterilize an entire generation by cutting them off from knowledge. This makes it imperative for all of us to ensure that Amhara children continue their education despite adversity. The survival of the nation depends on it.

**🛡️ Our Core Value: Education**

The Amhara Fano People's Organization (AFPO) upholds education as a core value—central to our vision for progress, dignity, and national resilience. Without education, the world remains in darkness. It is the light that empowers individuals, strengthens communities, and builds nations.

Education is not just a necessity—it is a guiding principle embedded in our draft manifesto and our movement's long-term goals.

**🎯 Our Commitment to Uninterrupted Continuation of Schooling**

As we approach the Ethiopian New Year 2018, we call for the uninterrupted continuation of schooling across the region. Our students deserve stability, opportunity, and the chance to thrive. AFPO pledges to do its part to ensure that schools remain open, safe, and conducive to learning.

✅ In areas under our control, we will ensure that everything runs smoothly.
✅ Our Fano fighters and leadership are fully aware of this priority, and the message has been clearly communicated through our chain of command.

**🚨 The Crisis of Educational Injustice**

For too long, Amhara students—both in the Amhara region and across Ethiopia—have faced deliberate and systematic marginalization by successive governments. This exclusion spans every level of education, from primary schools to colleges and universities, and includes:

- 📚 Denial of equal access to quality education
- 💻 Lack of modern learning resources and technology
- 🏫 Unsafe, discriminatory, and militarized learning environments.

Even in higher education, Amhara students are routinely denied opportunities, harassed, and excluded from academic advancement. Most disturbingly, Amhara women students have been kidnapped from university campuses, subjected to violence, and abandoned without protection or justice. These acts are not isolated—they reflect a broader pattern of neglect and abuse that has left generations of Amharas unable to compete with their peers in science, technology, and innovation.

This is not just an educational crisis—it is a human rights emergency.

🕊️ ***"We do not fight for one cause alone—we fight for the light in our children's eyes. For their right to learn without fear, to dream without limits, and to rise without chains. The injustice in education is a wound we cannot ignore, and for its healing, we give our all."***
*— paraphrased from the speeches of the late Major General Wubante Abate*

The injustice in the education system is one of the many reasons our Fano fighters are paying the ultimate sacrifice. We are fighting for the dignity and future of our children. Our sacrifice is a call to action: to restore justice, to protect opportunity, and to ensure that every student can learn without fear, discrimination, or exclusion.

**📚 Why Education Matters More Than Ever**

In today's rapidly evolving world, education is not just about literacy—it's about equipping our youth with the tools to innovate, lead, and compete globally. The rise of artificial intelligence, robotics, biotechnology, and digital economies demands a new generation of thinkers and creators.

No Amhara student should be left behind—and no Ethiopian student, in any region, should be denied the opportunity to learn, grow, and compete globally. Every child deserves the chance to become an engineer, scientist, coder, doctor, or entrepreneur. They deserve access to computers, internet connectivity, STEM programs, and mentorship. They must be able to stand shoulder-to-shoulder with other Ethiopians and international students in their age groups—whether in Addis Ababa, Nairobi, Berlin, or Boston.

**🧱 Resilience Amid Repression**

Even under this repressive government—which continues to target Amhara communities using full military force, including drones and heavy artillery—our students refuse to be broken. From urban centers to the most remote rural villages, Amhara youth demonstrate extraordinary hope, creativity, and innovation.

Despite the trauma, displacement, and systemic exclusion, they continue to:

- 🧠 Build solutions with limited resources
- 💡 Innovate in science and technology
- 📖 Pursue education under threat of violence
- 💛 Support one another in solidarity and courage

Their brilliance is not a miracle—it is a testament to the strength of a people who have been denied everything yet still rise. This generation deserves global support, protection, and investment—not silence.

**📢 A Call to Citizens and the Global Community**

We call upon our people —both within Ethiopia and across the diaspora—to stand with our students and teachers. Support them in every way possible: through resources, advocacy, mentorship, and solidarity. The future of our people depends on the education of our youth.

We also respectfully urge international organizations, humanitarian agencies, and the diplomatic community to recognize the urgent need for educational equity and protection in the Amhara regions and beyond. We invite your support in safeguarding the right to education, providing resources, and amplifying the voices of marginalized students and educators. Your engagement can make a lasting impact.

✨ Let This New Year Be a Turning Point

✨ Let it be a year of light, learning, and liberation.

**Victory to the Amhara People.**

**Peace for Ethiopia**

**August 20, 2025**

**Ethiopia**

## ርዕሰ አንቀጽ

### በአዲሱ የኢትዮጵያ ዓመት (2018) የትምህርት ሂደትን በተመለከተ የአፋሕድ የአቋም መግለጫ

**ትምህርት ካለመስተጓጎል እንዲቀጥል ለማስቻል ዓለማቀፋዊ የድጋፍ ጥሪ**

ትምህርትና ትምህርት ቤት በጦርነት ወቅት ለብዙ ችግር የሚጋለጡ ህጻናትን ስነ-ልቦና መጠበቂያ ተቋም ነው። በራሳቸው ነገሮችን ማገናዘብ ለማይችሉ ታዳጊዎች የምክር፣ የስነ ልቦና እና የጥንካሬ ተምሳሌትን የሚማሩበት ተቋም ስለሆነ በጦርነትና ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሁሉም የአማራ ልጆች ትምህርት የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት። ጨፍጫፊና ጸረ አማራ የሆነው የአብይ አገዛዝ ላለፉት ሁለት አመታት መላ አማራን የጦርነት አውድማ አድርጎ በመቆየቱ ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአማራ ህፃናትና ወጣቶች ከትምህርት ገበታ ውጭ ሆነው ለከፍተኛ የስነ-ልቦና ቀውስ ከመዳረጋቸውም በላይ እንደ ትውልድ ወደኋላ እንዲቀሩ ተደርጓል፡፡ አገዛዙ ትምህርት ተቋማትን በድሮንና በከባድ መሳሪያ ከመደብደቡም በላይ ትምህርት ቤቶችን ወታደራዊ ካምፕ በማድረጉ የትምህርት ቁሳቁሶች እንዲወድሙና በተራዛሚ ጦርነት የአማራን ህዝብ በድንቁርና እና በኋላቀርነት ለማስቀረት የታሰበ ሴራ መሆኑ ግልጽ ነው።

አሁን ያለው ጦርነት ተቋጭቶ ሌላ ስርዓት ሲመጣ የማህበረሰብ መልሶ ግንባታ ባለቤት መሆን የሚችል የተማረ ትውልድ ሜዳ ላይ ማግኘት አንችልም። ነገ የምናጭደው ዛሬ የዘራነውን ነውና፡፡

በአውሮፓ የነበሩ አይሁዶች ከሂትለር ጭፍጨፋ ሸሽተው ጫካ እየተዋጉ ባሉበት ሰዓት መሬት እየቆፈሩ (በጉድጓድ ውስጥ) ትምህርት ቤት ይሰሩ ነበር። በየቀኑ በሚፈፀም የአየር ድብደባ እየፈረሰባቸውም እንኳን በጽናት ትምህርትን ያስቀጥሉ ነበር። የህዝባችን እሴት መጠበቅ የምንችለው በትምህርት ቤት በኩል ነው ብለው ያምናሉ። የትምህርት ቤት እና የትምህርትን ሚና ፊደል ከመቁጠር፣ ከመጻፍ እና ማንበብ ባሻገር መሆኑን ማሰብ ያስፈልጋል። በአማራ ላይ እየተፈፀመ ያለው መንግስት መር ጦርነት ከሞትና ከስደትም በላይ ትውልዱን መካን ለማድረግ የታሰበ ሴራ መሆኑን በመረዳት በማይመች ሁኔታ ውስጥም ሆኖ የአማራ ልጆች ትምህርት እንዲቀጥሉ ለማድረግ ሁሉም ቆርጦ መነሳት ይኖርበታል፡፡

🛡️ ዋና እሴታችን፡ ትምህርት

የአማራ ፋኖ ህዝባዊ ድርጅት ትምህርት የእድገታችን፣ የክብር እና የአገራዊ ፅናት ራዕያችን መሠረት በመሆኑ እንደ ዋና እሴቱ ይቀበለዋል — ካለትምህርት ዓለም በጨለማ ትመሰላለች። ትምህርት ለግለሰቦች ዕውቀት የሚያበራ በመሆኑ፣ ትምህርት ማህበረሰቦችን የሚያጠነክር እና ሀገርን የሚገነባ ነው።

ጥራት ያለው ትምህርት አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን - በረቂቅ ማኒፌስቶአችን እና በንቅናቄያችን የረጅም ጊዜ ግቦች ውስጥ የተካተተ መመሪያ ነው።

🎯 ያለማቋረጥ ትምህርትን ለማስቀጠል ያለን ቁርጠኝነት

የኢትዮጵያ አዲስ አመት 2018 ዓ.ም እየተቃረበ ሲመጣ፣ በመላ ክልሉ ካለምንም መስተጓጎል ትምህርት እንዲቀጥል እንጠይቃለን። ተማሪዎቻችን ተረጋግቶ የመማር እና የማደግ እድል ይገባቸዋል። አፋሕድ ትምህርት ቤቶች ክፍት፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ለመማር ምቹ ሆነው እንዲቀጥሉ የበኩሉን ለመወጣት ቃል ገብቷል።

✅ በእኛ ቁጥጥር ስር ባሉ አካባቢዎች የትምህርት ሂደት ካለችግር እንዲካሄድ ለማድረግ ኃላፊነት ወስደን ለመስራት ዝግጅት ላይ እንገኛለን።

✅ የፋኖ ታጋዮቻችን እና አመራሮቻችን ይህንን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሲሆን መልእክቱ በዕዝ ሰንሰለታችን እስከታችኛው መዋቅር በግልፅ ተላልፏል።

🚨 የትምህርት ኢፍትሃዊነት ቀውስ

ለረጅም ጊዜ የአማራ ተማሪዎች - በአማራ ክልልም ሆነ በመላው ኢትዮጵያ - በተከታታይ መንግስታት ሆን ተብሎ እና ስልታዊ ማግለል ገጥሟቸዋል። ይህ መገለል ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከ ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች ያሉትን ሁሉንም የትምህርት ደረጃዎች ያጠቃልላል። በተለይም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

📚 ትምህርት በጥራትና በእኩል ተጠቃሚነት እንዳይዳረስ መከልከል፣

💻 የዘመናዊ የትምህርት ግብአቶች እና ቴክኖሎጂ መቋረጥ፣

🏫 በደህንነት እጦትና በአድሎአዊ የጸጥታ መጓደል የተጎዱ የመማሪያ አካባቢዎች፣

🟫 በርካታ የዳስ ትምህርት ቤት ሆነው መቅረታቸውና በጭቃ የተሰሩትም የፈራረሱ መሆናቸው፣

በከፍተኛ ትምህርትም ቢሆን የአማራ ተማሪዎች እድሎች እየተነፈጉና እድሉን ያገኙትም እየተንገላቱ እና ከአካዳሚክ እድገት እንዲርቁ ይደረጋሉ። ከሁሉም በላይ የሚያስጨንቀው የአማራ ሴት ተማሪዎች ከዩኒቨርስቲ ግቢ ታፍነው ተወስደዋል፣ ጥቃት ይደርስባቸዋል፣ አሁንም ያለ በቂ ጥበቃና ፍትህ ቀርተዋል። እነዚህ ድርጊቶች የተነጠሉ ክስተቶች አይደሉም፤ ታቅደውና በተከታታይነት የሚሆኑ እንጂ። በዚህም ምክንያት ተከታታይ የአማራ ትውልዶች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና በአዳዲስ ፈጠራዎች ከእኩዮቻቸው ጋር ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ተደርገዋል።

ይህ የትምህርት ቀውስ ብቻ አይደለም - አስቸኳይ ትኩረት የሚሻ የሰብአዊ መብት አደጋ ጭምር እንጂ።

🕊️ *"እኛ የምንታገለው ለአንድ ዓላማ ብቻ አይደለም - በልጆቻችን ዓይን ውስጥ ላለው ብርሃን እንታገላለን። ያለ ፍርሃት መማር እንዲችሉ፣ ያለ ገደብ ህልምና ራዕይ እንዲኖራቸውና በራሳቸው የመተማመን አቅም እንዲያዳብሩ ጭምር ነው። በትምህርት ላይ ያለው ኢፍትሃዊነት ችላ የማንለው ቁስል ነው፣ ዘላቂ መፍትሔ እስኪመጣ ድረስ የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ እንከፍላለን"* ከሜጀር ጄኔራል ውባንተ አባተ የትግል ወቅት ንግግሮች (ቃል በቃል ያልሆነ)።

የፋኖ ታጋዮቻችን የመጨረሻውን መስዋዕትነት እየከፈሉ ካሉባቸው በርካታ ምክንያቶች አንዱ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ያለው ኢፍትሃዊነት ነው። የእኛ መስዋዕትነት የተግባር ጥሪ ነው፡ ፍትህን ለማንበርእና እያንዳንዱ ተማሪ ያለ ፍርሃት፣ አድልዎ እና መገለል እንዲማር ማረጋገጥ ነው።

📚 ትምህርት ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

ዛሬ በፍጥነት በማደግ ላይ ባለ ዓለም፣ ትምህርት ማንበብና መጻፍ ብቻ አይደለም - ወጣቶቻችንን ለመፈላሰፍ፣ ለመምራት እና በአለም አቀፍ ደረጃ ለመወዳደር የሚያስችላቸውን መሳሪያዎችን ማስታጠቅ ጭምር ነው። የሰው ሰራሽ አስተውሎት፣ የሮቦት ቴክኖሎጂ፣ የስነ ሕይወት እና የዲጂታል ምጣኔ ሀብት እድገት አዲስ የአስተሳሰብ እና ፈጠራ ባለቤት የሆነ ትውልድ ይፈልጋል።

የትኛውም የአማራ ተማሪ ወደ ኋላ መቅረት የለበትም - የትኛውም ኢትዮጵያዊ ተማሪ በየትኛውም ክልል ውስጥ በአለም አቀፍ የጥራት ደረጃ የመማር፣ የማደግ እና የመወዳደር እድል ሊነፈግ አይገባም ብለን እንደምናምነው ሁሉ። እያንዳንዱ ልጅ መሐንዲስ፣ ሳይንቲስት፣ ዶክተር ወይም ስራ ፈጣሪ የመሆን እድል ሊሰጠው ይገባዋል። ኮምፒውተሮችን፣ የበይነመረብ ግንኙነትን፣ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምህንድስናና የሂሳብ (STEM) ፕሮግራሞችን እና አማካሪዎችን ማግኘት ይገባቸዋል። በአዲስ አበባ፣ በናይሮቢ፣ በበርሊን ወይም በቦስተን ካሉ ሌሎች ኢትዮጵያውያን እና አለም አቀፍ ተማሪዎች ጋር ተወዳዳሪ መሆን ይገባቸዋል።

🟫 በጭቆና መካከል በፅናት መቆም

የአማራን ህዝብ ሰው አልባ አውሮፕላኖችን እና ከባድ መሳሪያዎችን በመጠቀም በግዙፍና በተሟላ ወታደራዊ ኃይል በሚደበድብ በዚህ ጨቋኝ መንግስት ወረራ ሥር ሆነውም ተማሪዎቻችን ሊሰበሩ ፈቃደኛ አይደሉም። የአማራ ወጣቶች ከከተሞች በጣም ርቀው በሚገኙ የገጠር መንደሮች ሳይቀር እጅግ የላቀ የፈጠራ ስራን አሳይተዋል።

ምንም እንኳን ጉዳቱ፣ መፈናቀሉ እና ስርአታዊ መገለሉ አስከፊ ቢሆንም፤

🧠 በውስን ሀብቶች መፍትሄዎችን እያመነጩ፣

💡 በሳይንስና በቴክኖሎጂ ፈጠራ እየተሳተፉ፣

📖 በጥቃት ስጋት ውስጥ ትምህርትን እየተከታተሉ እና

🤝 በመተባበር እና በድፍረት እርስ በርስ እየተደጋገፉ መቀጠል ምርጫ የሌለው ጉዳይ ነው።

አእምሮአዊ ብሩህነታቸው በተአምር የሆነ አይደለም - ሁሉን ነገር ቢነፈጉም በዚህ ሁሉ መሃል ከፍ እያለ ላለው ሕዝብ ጥንካሬ ማሳያ እንጂ። ይህ ትውልድ ዝምታ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ፣ ጥበቃ እና ፍትህ ይገባዋል።

📢 ለኢትዮጵያውያንና ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ጥሪ

በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በዲያስፖራ የሚገኙ ወገኖቻችን በችግር ውስጥ ትውልድ ለማስቀጠል ጥረት ከሚያደርጉ መምህራንና ተማሪዎቻችን ጎን እንዲቆሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በሚችሉት መንገድ ሁሉ በወገናዊ ስሜት በግብአት፣ በአማካሪነት፣ቴክኖሎጅ ደጋፍ እና በሌሎችም ዘርፎች ድጋፍ ታደርጉ ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን። የህዝባችን የወደፊት እጣ ፈንታ በወጣቶቻችን ትምህርት ላይ የተመሰረተ ነው።

እንዲሁም አለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ግብረሰናይ ተቋማት እና የዲፕሎማሲ ማህበረሰቡ በአማራ ክልል እና በሌሎች አካባቢዎች ፍትኃዊ የትምህርት ስርጭት እና ጥበቃ ይኖር ዘንድ ጫና እንዲያሳድሩ በአክብሮት እናሳስባለን። የትምህርት መብትን በማስጠበቅ፣ ግብዓቶችን በማቅረብ እና የተገለሉ ተማሪዎችን እና አስተማሪዎችን ድምጽ በማጉላት ድጋፍ ያደርጉ ዘንድ እንጠይቃለን - ድጋፋችሁና ተሳትፎአችሁ ዘላቂ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላልና።

✨ ይህ አዲስ አመት የለውጥ መታጠፊያ ዘመን ይሁንልን!

✨ የብርሃን፣ የመማሪያ እና የነጻነት ዓመት ይሁንልን!

ድል ለአማራ ህዝብ!

ሰላም ለኢትዮጵያ!

ረቡዕ ነሐሴ ፲፬ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.

ኢትዮጵያ